Amharic I አማርኛ

# የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዝገባ ለ2027



ፋውንዴሽን (ፕሬፕ/መሰናዶ በመባልም ይታወቃል) በቪክቶሪያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ አመት ነው።

ልጅዎ ከኤፕሪል 30 2027 በፊት 5 አመት ከሞላው ትምህርት መጀመር ይችላል።
ልጅዎ 6 ዓመት ሲሞላው ትምህርት ቤት ግዴታ ነው።

### መቼ ማመልከት እችላለሁ?

ለ 2027 በቪክቶሪያ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ለማመመልከት፡-

- ከሰኞ 20 ኤፕሪል 2026 ጀምሮ **ክፍት ይሆናል**
- እስከ አርብ ጁላይ 31 ቀን 2026 ድረስ **ይጠናቀቃል።**

### የልጄ የምዝገባ መብቶች ምንድን ናቸው?

በቪክቶሪያ ውስጥ፣ *በትምህርት እና ስልጠና ማሻሻያ ህግ 2006* መሰረት ልጅዎ በተሰየመው የአጎራባች ትምህርት ቤት (የእርስዎ 'የአካባቢ ትምህርት ቤት') የመማር መብት አለው። የአከባቢዎ ትምህርት ቤት በቋሚ የመኖሪያ አድራሻዎ የትምህርት ቤት ዞን ይወሰናል። የምዝገባ ውሳኔዎች እንዴት እንደሚወሰኑ የበለጠ ለማወቅ፣ [ትምህርት ቤት መመዝገብ] የሚለውን ይጎብኙ።

### ልጄን በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ አመት እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?

ልጅዎን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ አመት እንዴት ማስመዝገብ እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃ እነሆ፡-

1. **የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ያግኙ**
   የአካባቢዎን የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም በአቅራቢያ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ለማግኘት www.findmyschool.vic.gov.au ይጎብኙ።
2. **ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ**
   አማራጭ ጉብኝት ለማስያዝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ። ትምህርት ቤቱ በኦንላይን (VicStudents) ወይም በወረቀት ላይ የተመሰረተ የምዝገባ ሂደትን ይጠቀም እንደሆነ ያረጋግጡ። ይህ መረጃ በትምህርት ቤቱ ድረ-ገጽ በኩል ይገኛል።
3. **የመረጃ ጥቅል ያውርዱ**
   ፋውንዴሽን (መሰናዶ) የምዝገባ መረጃ ጥቅል [ከፋውንዴሽን መመዝገቢያ (መሰናዶ) (Enrolling in Foundation (Prep))] ያውርዱ። ጥቅሉ እስከ ሐሙስ ኤፕሪል 2 ቀን 2026 ድረስ ይገኛል።
4. **የምዝገባ ማመልከቻዎን ያስገቡ**
   የምዝገባ ማመልከቻ **እስከ አርብ ጁላይ 31 ቀን 2026** በኦንላይን (VicStudents) ወይም በድረገጻቸው ላይ በተገለጸው የትምህርት ቤት ሂደት መሰረት የወረቀት ቅጹን በመጠቀም ያስገቡ።
5. **ውጤትን ይቀበሉ**
   **ከሰኞ ኦገስት 3 እስከ አርብ ኦገስት 14 ቀን 2026** ባለው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻዎ ውጤት ማሳወቂያ ይደርሰዎታል። የምዝገባ እድል ከተሰጥዎት **እስከ አርብ ኦገስት 28 ቀን 2026 ድረስ** መቀበል አለብዎት።
6. **ለልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት መሸጋገር ይዘጋጁ**
   በ ተርም 4፣ 2026 ወቅት በሚደረጉ የተማሪ ሽግግር ክፍለ ጊዜያት ይሳተፉ። ልጅዎ ከ**ሐሙስ ጃንዋሪ 28 ቀን 2027** ጀምሮ ፋውንዴሽን ይጀምራል።

## የአካባቢዬን ትምህርት ቤት እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ከታች ያሉትን ቅደም ተከተሎች በመከተል የአካባቢዎን ትምህርት ቤት፣ ትምህርት ቤቴን ፈልግ (Find my School) ድህረ ገጽ ላይ ያግኙ፡-

1. www.findmyschool.vic.gov.au ወደ አሳሽዎ ያስገቡ።
2. ቋሚ የመኖሪያ አድራሻዎን 'Enter your address to get started' በሚለው ስር ያስገቡ።
3. 'Enrolment year' በሚለው ስር 2027ን ይምረጡ። **የ2027 የትምህርት ቤት ዞኖች እስከ ሐሙስ ኤፕሪል 2 ቀን 2026** ድረስ ይገኛሉ።
4. 'School type' ወይም 'የትምህርት ቤት አይነት' በሚለው ስር የመጀመሪያ ደረጃን ይምረጡ።

ከዚያም ካርታው አድራሻዎን፣ የአከባቢዎን ትምህርት ቤት እና በግራ በኩል ደግሞ የትምህርት ቤቱን አድራሻ ያሳያል። መጠቆሚያውን ወደ ታች ካንከባለሉት ወይም ስክሮል ካደረጉት ደግሞ ለአድራሻዎ ቅርብ የሆኑትን አምስቱን ትምህርት ቤቶች ያሳይዎታል። እንዲሁም በትምህርት ቤት ስም 'ትምህርት ቤት ፈልግ/Search for school' በሚለው ስር መፈለግ ይችላሉ።

## የምዝገባ ማመልከቻዬ ካልተሳካስ?

ማመልከቻዎ ካልተሳካ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- ወደ ሌላ ትምህርት ቤት **ያመልክቱ**። ልጅዎ በአካባቢዎ ትምህርት ቤት ቦታ የማግኘት ዋስትና አለው። የልጅዎን የአካባቢ ትምህርት ቤት ለማግኘት **ትምህርት ቤቴን ፈልግ/Find my School** የሚለውን ይጎብኙ።
- ውሳኔውን ይግባኝ ይበሉ። የፋውንዴሽን (ዝግጅት) መመዝገቢያ/ Enrolling in Foundation (Prep) ገጽ የምዝገባ ማመልከቻ ውጤት ይግባኝ ለማለት ባለው ሂደቱ ላይ መረጃ አለው።

## የምዝገባ የጊዜ ገደቦች ካለፉብኝ ምን ይሆናል?

ከ**ሰኞ ኤፕሪል 20 ቀን 2026** ጀምሮ በማንኛውም ጊዜ ልጅዎን ለ2027 የትምህርት ዘመን ፋውንዴሽን ለማስመዝገብ ማመልከት ይችላሉ።

ምንም እንኳን እስከ **አርብ ጁላይ 31 ቀን 2026** ድረስ የምዝገባ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ቢጠየቁም፣ የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ካመለጣቸው ቤተሰቦች፣ ቋሚ መኖሪያ አድራሻ ከቀየሩ ቤተሰቦች ወይም ወይም አዲስ ወደ ቪክቶሪያ ከመጡ ቤተሰቦች የዘገዩ ማመልከቻዎች አሁንም እንቀበላለን።

**ከጁላይ 31 ቀን 2026 በኋላ የገቡ** የምዝገባ ማመልከቻዎች በመምሪያው የምዝገባ ፖሊሲ መሰረት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከቻውን **በተቀበልንበት ቅደም ተከተል** የሚስተናገዱ ናቸው።

## የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለመመዝገብ ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?

ስለ ፋውንዴሽን ምዝገባ ሂደት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በአካባቢዎ የሚገኘውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መጠየቅ ይችላሉ።

ከ**ሰኞ ኤፕሪል 20 ቀን 2026** ጀምሮ በፋውንዴሽኑ ምዝገባ ሂደት ላይ የመረጃ ጥቅል በፋውንዴሽን ምዝገባ (ፕረፕ/መሰናዶ) ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

የመረጃ ጥቅሉን ለመተርጎም እገዛ ከፈለጉ፣ እባክዎን ለእርዳታ በአካባቢዎ የሚገኘውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## ለእርዳታ ማንን አነጋግራለሁ?

ለማመልከት የምትፈልጉት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሽግግር አስተባባሪ፣ የምዝገባ ኦፊሰር ወይም ርእሰ መምህር ስለምዝገባ ሂደቱ ሊኖርዎት የሚችል ማንኛውም አይነት ጥያቄ ሊረዳዎት ይችላል።

## ጠቃሚ ማገናኛዎች (ሊንኮች)

ልጅዎ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሲጀምር ለእርስዎ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ጠቃሚ ማገናኛዎችን ከዚህ በታች ይመልከቱ፡-

ትምህርት ቤቱን ፈልግ - findmyschool.vic.gov.au

የትምህርት ቤት ዞኖች መረጃ - vic.gov.au/school-zones

በፋውንዴሽን (መሰናዶ) መመዝገብ - vic.gov.au/enrolling-foundation-prep

በትምህርት ቤት መመዝገብ – vic.gov.au/how-choose-school-and-enrol

የአካል ጉዳት እና አካታች ትምህርት - vic.gov.au/disability-and-inclusive-education

የክልል ቢሮ አድራሻዎች - vic.gov.au/office-locations-department-education

# ለ2027 ፋውንዴሽን (ፕሬፕ/መሰናዶ) ምዝገባዎች የጊዜ ሰሌዳ

| የ 2026 ቀናት | ወላጆች/ተንከባካቢዎች ምን ማድረግ አለባቸው? |
|---|---|
| **ተርም 1** | **ማክሰኞ ጃንዋሪ 27 (ተማሪዎች ጃንዋሪ 28 ይጀምራሉ) እስከ ሐሙስ ኤፕሪል 2 ቀን 2026** |
| **ተርም 1 እና 2፣ 2026** | • በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተዘጋጁ *(አማራጭ)* **የትምህርት ቤት ጉብኝቶች ላይ ይሳተፉ።** |
| **ሐሙስ 2 ኤፕሪል 2026** | • የ2027 የትምህርት ዘመን የትምህርት ዞኖች ይገኛሉ። የአካባቢዎን ትምህርት ቤት በ [www.findmyschool.vic.gov.au](http://www.findmyschool.vic.gov.au) **ማግኘት** ይችላሉ። |
| **ተርም 2** | **ከሰኞ ኤፕሪል 20 እስከ አርብ ጁን 26 ቀን 2026** |
| **ከሰኞ 20 ኤፕሪል 2026 ጀምሮ** | • ከተርም 2 መጀመሪያ ጀምሮ፣ ትምህርት ቤትዎ በሚሰጠው ምክር ላይ በመመስረት – በኦንላይን ወይም በምዝገባ መረጃ ጥቅል ውስጥ ያለውን የማመልከቻ ቅጽ በመጠቀም **የልጅዎን ማመልከቻ ይሙሉ እና ያስገቡ።**<br>• ለተጨማሪ ዝርዝሮች [በፋውንዴሽን (ፕሬፕ/መሰናዶ) መመዝገብ](#) **ከሚለው** የምዝገባ መረጃ ጥቅሉን ማውረድ ይችላሉ። |
| **ተርም 3** | **ሰኞ ጁላይ 13 እስከ አርብ መስከረም 18 ቀን 2026** |
| **አርብ ጁላይ 31 ቀን 2026** | • በሚከተለው ቀን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት **የተጠናቀቀውን ማመልከቻዎን ያስገቡ።** |
| **በሰኞ ኦገስት 3 እና በአርብ ኦገስት 14 ቀን 2026 መካከል** | • **የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች** በዚህ ጊዜ ውስጥ **የምዝገባ ውጤቶችን በጽሁፍ ያሳውቅዎታል።**<br>• ማመልከቻዎ ካልተሳካ፣ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ። |
| **በ አርብ ኦገስት 28 ቀን 2026** | • ከምዝገባ አቅርቦት ጋር የቀረበውን የምዝገባ ቅጽ በመሙላት፣ **የልጅዎን ቦታ ተቀባይነት ማግኘቱን ያረጋግጡ።**<br>• ይግባኝ ለማለት ካሰቡ፣ እስከ አርብ ኦገስት 28 ድረስ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትዎ የጽሁፍ ይግባኝ ያቅርቡ። |
| **በ አርብ መስከረም 11 ቀን 2026** | • የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የይግባኝ ውጤቶችን በጽሁፍ ያሳውቅዎታል። |
| **እስከ አርብ መስከረም 18 2026** | • ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትዎ ያቀረቡት ይግባኝ ካልተሳካልዎት፣ ለሚመለከተው የክልል ዳይሬክተር የጽሁፍ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ። |

| **ተርም 4** | **ሰኞ ጥቅምት 5 እስከ አርብ ዲሴምበር 18 ቀን 2026** |
|---|---|
| **ተርም 4፣ 2026** | • በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚስተናገዱ የሽግግር ክፍለ ጊዜዎች ላይ ይሳተፉ። |
| **እስከ አርብ 6 ህዳር 2026** | • ለክልሉ ዳይሬክተር ይግባኝ ካቀረቡ፣ ክልሉ በዚህ ቀን ውጤቱን በጽሁፍ ያሳውቅዎታል። ይህ የሚመለከተው አርብ ሴፕቴምበር 18 በሚዘጋበት ቀን የተቀበሉዋቸው ይግባኞች ብቻ ነው። |